# “የጥብቅና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች (Law Firms) አስፈላጊነት እና አስተዳደር” ላይ ትምህርታዊ ውይይት

**በኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር እና በመስፍን ታፈሰ የሕግ ቢሮ በመተባበር የተዘጋጀ**

ጥር 12/2010 ዓ.ም.
ኢሊሊ ኢንተርናሽናል ሆቴል

# የጥብቅና አገልግሎት ሰጪ አስፈላጊነት እና አስተዳደር

የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከመስፍን ታፈሰ የሕግ ቢሮ ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ ቅዳሜ ጥር 12/2010 ዓ.ም. ከአባላቱ እና ከሌሎች የሕግ ባለሙያዎች የተውጣጡ እና ጉዳዩ የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የተሳተፉበት የጥብቅና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች (Legal Firms) አስፈላጊነት እና አስተዳደር በሚል ርዕስ ከጠዋቱ 2:30-7:00 በኢ.ሊ.ሊ. ኢንተርናሽናል ሆቴል ውይይት አካሂዷል፡፡

ለውይይቱ መነሻ የሚሆነውን "Toughts on the Organization of Legal Practice in Ethiopia" በሚል ርዕስ ያዘጋጁትን ጽሑፍ ያቀረቡት አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁ ጠበቃና የሕግ አማካሪ ሲሆኑ አቶ መስፍን ታፈሰም ጠበቃና የሕግ አማካሪ "**የጥብቅና አገልግሎትን በሕግ ድርጅት አማካኝነት መስጠት፤ ለምን?**" በሚል ርዕስ ለውይይቱ መነሻ የሚሆን ጽሑፍ አቅርበዋል፡፡ ውይይቱን የመሩት አቶ ጌታቸው ቅጣው ጠበቃና የሕግ አማካሪ ናቸው፡፡

ውይይቱን በእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር የከፈቱት የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አቶ ቴዎድሮስ ምህረት የጥብቅና ሥራ በሀገሪቱ በግለሰብ ባለሙያዎች የሚሠራ ሥራ ሆኖ መቀጠሉን ነገር ግን ሩቅ ሳይኬድ እዚሁ አፍሪካ ውስጥ የቅርብ ጐረቤታችን በሆነችው ኬኒያ እንኳ የጥብቅና አገልግሎት በጥብቅና አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አማካኝነት እየተሰጠ መሆኑን በንግግራቸው አመልክተዋል፡፡ አቶ ቴዎድሮስ በዚሁ ንግግራቸው የዛሬ 18 ዓመት ገደማ የወጣው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥ እና ምዝገባ አዋጅ ቁ. 199/92 የጥብቅና ድርጅቶች ምዝገባና ፍቃድን የሚመለከት ድንጋጌ ማካተቱን አስታውሰው በተለይ አንቀፅ 18(4) የጥብቅና ድርጅቶች ፈቃድ አሰጣጥን በሚመለከት ዝርዝር መመሪያዎች እንደሚወጣ መደንገጉን ነገር ግን ለአለፉት 17 ዓመታት መመሪያው አለመውጣቱን በንግግራቸው አመልክተዋል፡፡ አያይዘውም የውይይቱ ዓላማም የተኛውን ይህንን ጉዳይ ለመቀስቀስና ወደፊት ለማራመድ መሆኑን በዚህ ረገድም በስብሰባው ላይ የተገኙ ወገኖች ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ በመጠየቅ ንግግራቸውን አጠቃልለዋል፡፡

በአወይይነት መድረኩን የያዙት አቶ ጌታቸው ቅጣው፣ የአቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁን እና የአቶ መሥፍን ታፈሰን ትምህርት እና የሥራ ልምድ በአጭሩ ለተሳታፊዎች ከአስተዋወቁ በኋላ አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁን የመወያያ ጽሑፋቸውን እንዲያቀርቡ በመጋበዝ ለተናጋሪው መድረኩን ለቀዋል፡፡

አቶ ታምሩ በስብሰባው ላይ የሚያቀርቡትን ጽሑፍ በሕግ ላይ ያተኮሩ የምርምር ውጤቶችን በሚያትም በ"Mizan Law Review" ጆርናል ላይ መታተሙን፣ በገለፃቸውም ላይ የሚያነሷቸው ዓበይት ነጥቦች በተጠቀሰው ጆርናል ላይ የተነሱ መሆናቸውን እንደሚሆኑ ነገር ግን ውይይቱን ባዘጋጀው አካል የጥብቅና ድርጅቶችን ታሪካዊ ዳራ እንዲዳስሱ በመጠየቃቸው ታሪካዊ ዳራው ባጭሩ ለማቅረብ እንደሚሞክሩ ለተሳታፊዎች አስታውቀዋል፡፡

ጆን ሎክን፣ ዢን ዣክ ሩሶን የመሳሰሉ ፈላስፋዎች ኅብረተሰብ አንዱ ሌላውን ለማጥቃትና በኃይሉና በጉልበቱ ተመክቶ ከሚኖርበት State of Nature የኅብረተሰብ እድገት ሰላም ወደሰፈነበት እና በሕግ ወደሚመራ አኗኗር ቀስ በቀስ እና አዝጋሚ በሆነ የለውጥ ሂደት በእንግሊዝኛው "Rule of the Jungle" በአማርኛና "በፈረሰ አንገት በሠይፍ አንደበት" ከሚለው አስተሳሰብ ወደ "ዳኛ አውጥቶ ዘንግ አቅንቶ" ወደሚለው አስተሳሰብ መሸጋገሩን፣ በዚህም መጀመሪያ ሥርዓት ቀጥሎም ሕግ መምጣቱን በጽሑፋቸው መንደርደሪያ ላይ ገልፀዋል፡፡

ጽሑፍ አቅራቢው ዘመናዊ ሕግ ወደ ኢትዮጵያ የገባበትን ሁኔታ ሲያስታውሱም የአድዋ ጦርነት ኢትዮጵያን ከዓለም አቀፍ ሕግ ጋር ያስተዋወቀ ዓይነተኛ ክስተት መሆኑን፣ የአድዋ

ጦርነትን ተከትሎ የተለያየ የዓለም መንግሥታት የቆንስላ ጽ/ቤቶችን በኢትዮጵያ ለማቋቋም፣ የተለያዩ እምነት መሪዎች እና ነጋዴዎች ወደ ኢትዮጵያ ለመምጣት በር የከፈቱበት ወቅት እንደነበር፣ ጥር 2 ቀን 1900 ዓ.ም. ዳግማዊ አፄ ምኒሊክ የCapitulation Treatyን መሠረት በማድረግ የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ማቋቋማቸውን፣ ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ ዘመናዊ ሕግ እስክታወጣ ድረስ የናፓሊዮን ሕግ (ኮድስ) ተፈፃሚ እንዲሆን መስማማቷን አውስተዋል፡፡ ይህ ክስተት በኢትዮጵያ ላይ ያስከተላቸውን አንደምታዎች ሲገልፁም ዳኛ እና ጥብቅና ከዚህ አዲስ ክስተት ጋር ተያይዞ መምጣቱን፣ በጣሊያን ወረራ ጊዜም የጣሊያን ፍ/ቤቶች መቋቋማቸውን በዚህ ጊዜ ዘመናዊው ሕግ ከጥብቅና ሥርዓቱ ጋር ተያይዘው ወደ ኢትዮጵያ መምጣታቸውን፣ ነፃነት ከተመለሰ በኋላ በተለይ በ1934 የወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1934 የመጀመሪያ የዳኝነት ሥርዓትን የጥብቅና አገልግሎትን ማቋቋሙን፣ አዋጁ የCapitulation Treatyን እውቅና በመስጠት እስከ 1949 ዓ.ም. ድረስ የውጭ ሀገር ዳኞች እና የውጭ ሀገር ጠበቆች በኢትዮጵያ ፍርድ ቤቶች እንዲሠሩ ያደረገ አዋጅ መሆኑን፣ በተለይም በ1992 አዋጅ ቁ. 1999/1992 እስከሚሻር ድረስ የውጭ ሀገር ጠበቆች በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች እንዲሠሩ የፈቀደ መሆኑን፣ ይህ አዋጅ ከወጣ በኋላ የውጭ ሀገር ጠበቆች በኢትዮጵያ ፍ/ቤቶች የማይቆሙ መሆኑን አቶ ታምሩ አመልክተዋል፡፡

ከ1934-1965 ዓ.ም. ድረስ የነበሩ ክርክሮችና ውሳኔዎችን ያስታወሱት ጽሑፍ አቅራቢው እጅግ የሚያስገርሙ እና የሕግ ሳይንሱን የማዳበር አቅም ያሏቸው እንደነበሩ፣ በዚያ ዘመን በጠበቆች ዘንድ የአበረውም አስተሳሰብ አንድ ጠበቃ በሁሉም የሕግ ዘርፎች የተዋጣለት አገልግሎት መስጠት እንደማይችል፣ ሁሉንም የሕግ ዘርፎች መነካካት ከዘመናዊም የጥብቅና አሠራር ጋር አብሮ የማይሄድ መሆኑ በቂ ግንዛቤ የተያዘበት እንደነበር አመልክተዋል፡፡ ይህንን ድምዳሜያቸውን በተጨበጠ ማስረጃ ያስደገፉት አቶ ታምሩ በዚያ ዘመን scot & scot የሚባል እና በአሜሪካን ጠበቆች የሚመራ የጠበቃ ድርጅት፣ ሳሊኮስ የሕግ ቢሮ በጣሊያናዊ የሕግ ባለሙያ የሚመራና አሁን በሕይወት የሌሉት አቶ ዓለማየሁ እሸቴ ተባባሪ ሆነው ይሠሩ የነበሩትን፣ ሀማዊ የሚባልና በሊባኖሳዊ ዜጋ የሚመራ አቶ አጥናፍ ፀሐይ በተባባሪነት የሚሠሩበት የሕግ ቢሮ፣ በተፈሪ እና በቀለ የሕግ ቢሮ አሁን በሕይወት የሌለው አቶ ግርማ ታደሰ ተባባሪ የነበረበት፣ በአቶ ሰላሙ በቀለ፣ ታደለ ድልነሳሁ፣ ኬና ጉማ እና ዳንኤል ዘለቀ ትብብር ይካሄድ የነበረው የሕግ ቢሮ፣ አቶ ኀለ ሚካኤል ባሕታ የሕግ ቢሮ ከበደ ፍስሃን የመሳሰሉ ጠበቆች በተባባሪነት የሠሩበት፣ ጌታሁን ሁነኛው የሕግ ቢሮን እንዲሁም ፍስሐ እና ታደሰ የሕግ ቢሮን ለአብነት በማብራራታቸው ላይ አንስተዋል፡፡

ይህ በጐ ጅምር በ1966 ዓ.ም. በተቀሰቀሰ ሕዝባዊ አብዮት እና እሱን ተከትሎ አገሪቱ የተቀበለችው የጀመረችው የሶሻሊስ ርዕዮተ ዓለም የግል ሀብት ባለቤትነት የማያበረታታ ስለነበር ተቋቁመው የነበሩት የdefacto የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቶች መክሰማቸውን አቶ ታምሩ በጽሑፋቸው አመልክተዋል፡፡ አያይዘውም የdefacto አሠራር እንደገና ማንሰራራት የጀመረው ከ1983 ዓ.ም. የመንግሥት ለውጥ በኋላ እንደነበር በዚህ ረገድም ግንባር ቀደም የነበሩት አበበ ወርቁ፣ አለሙ ደነቀው፣ ኮማንደር ኃይሉ መኮንን እና ዳንኤል በቀለ እንደነበሩ፣ እነዚህ ባለሙያዎች ያቋቋሙትን defacto የጠበቃ ድርጅት በጊዜው በነበረው የንግድ ሚኒስቴር በንግድ ሕጉ መሠረት በኃላፊነት የተወሰነ የሽርክና ማኅበር እንዲመዘግብላቸው ማመልከቻ ማስገባታቸውን፣ የሚኒስቴር መ/ቤቱ ለመመዝገብ ፈቃደኛ እንደነበር፣ ነገር ግን በጊዜው የፍትሕ ሚኒስቴር ድርጊቱ ሕገ-ወጥ መሆኑን ጠቅሶ ክሊራንስ ላለመስጠት መወሰኑን፣ የጠበቆቹም ፈቃድ ለጊዜው መታገዱን፣ ውሳኔው እንዲህ ዓይነት ሃሳብ ለነበራቸው ጠበቆች የማስጠንቀቂያ መልዕክት ማስተላለፉን አቶ ታምሩ አስታውሰው ይህንን ውሳኔ በማነፃፀር በ1960ዎቹ የጠበቃ ድርጅትን ለማቋቋም በዘመኑ ለነበረው የፍትሕ ሚኒስቴር ይቀርቡ የነበሩ ጥያቄዎች ይሰጥ ከነበረው “አይቻልም” ከሚል ምላሽ ጋር በማነፃፀር ከ30 ዓመታት በኋላ ለቀረበው ተመሳሳይ ጥያቄ የፍትሕ

ሚኒስቴር የሰጠው ምላሽ መመዝገብ አትችሉም ከማለት ባሸገር ጥያቄ ያቀረቡትን ጠበቆች ፈቃድ ለጊዜውም ቢሆን ማገዱ አስገራሚ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

በኢትዮጵያ ሕግ ጠበቆች ተደራጅተው አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉባቸው እድሎች ሙሉ በሙሉ የተዘጋ እንደነበር የገለፁት አቶ ታምሩ የ1952 የኢትዮጵያ ንግድ ሕግ የተለያዩ ማኅበራት ማለትም የኅብረት የሽርክና ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር፣ የሽርክና ማኅበራትን የያዙ ድንጋጌዎችን ማካተቱን በዋቢነት በመጥቀስ በሌሎች አገሮች እነዚህ ዓይነቶቹ ተቋማት ላይ አነስተኛ ማሻሻያ ተደርጕባቸው የጠበቆች ድርጅቶችን ማቋቋም መቻሉን አቶ ታምሩ አብራርተዋል፡፡ አያይዘውም በኢትዮጵያ ያሉ ጠበቆች እነዚህን በንግድ ሕጉ የተደነገጉ የማኅበራትን ተጠቅመው የጠበቆች ድርጅቶችን ማቋቋም ያልቻሉት በጠበቆች ዘንድ አርቆ ማስተዋል ካለመኖሩ በተጨማሪ የንግድ ሕጉ እና የሕግ አገልግሎት ሥራ አስተዳዳሩ በተለያዩ ሁለት መሥሪያ ቤቶች ማለትም በንግድ ሚኒስቴር እና በፍትሕ ሚኒስቴር የሚተዳደሩ መሆናቸው ሌላው እንቅፋት መሆኑን በገለፃቸው አመልክተዋል፡፡ ከሌሎቹ የሽርክና ማኅበራት ይልቅ ተራ የሽርክና ማኅበር በጠባዩ የንግድ ባሕሪ ስለሌለው የጥብቅና ድርጅትን ለመመሥረት ተስማሚ ቢሆንም ይህ ተቋም በጣም ልቅ በመሆኑ የጠበቆች ድርጅቶችን ለመመሥረት የሚያስችል የሚያስችል መሆኑን ይህም ክፍተት የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጠበቆች ፈቃድ አሰጣጥና ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 199/1992 አንቀፅ 18(2) የሚያቋቁመው (የጠበቆች) ድርጅት የንግድ ማኅበር ያልሆኑ ኃላፊነቱ ያልተወሰነ ማኅበር ነው፡፡ አቶ ታምሩ ይህ ድንጋጌ የንግድ ማኅበር አለመሆኑን ከመግለፁ ውጭ ከተራ የሽርክና ማኅበር የሚለየው ነገር እንደሌለ አስታውሰው ተራ የሽርክና ማኅበር ለጠበቆች ድርጅትነት ሞዴል ሆኖ ለማገልገል ተፈጥሮው እንደማይፈቅድ አስረድተዋል፡፡

አቶ ታምሩ ገለፃቸውን በመቀጠል በሌሎች ሃገሮች የLimited Liability Partnership (LLP) ሞዴል የጠበቆች ድርጅቶችን ለማቋቋም ዓይነተኛ መንገድ መሆኑን ጠቁመው ይህንን ሞዴልም በሀገራችን የጠበቆች ድርጅቶችን ለመመሥረት የማንጠቀምበት ምክንያት እንደሌለ ጠቁመዋል፡፡ አቶ ታምሩ የLLP ዓይነተኛ ጠባያትን ከዚህ እንደሚከተለው ዘርዝረዋል፡፡

- የሕግ ሰውነት ያለው መሆኑ፣
- ለረዥም ጊዜ ሊቀጥል የሚችል (Perpetual succession) መሆኑ፣
- በሸሪኮች መካከል የሚፈጠር ማናቸውም ለውጥ የተቋሙን/የድርጅቱን ሕልውና፣ መብቶች ወይም ኃላፊነቶች የማይለውጠው መሆኑ፣
- በመክሰስም ሆነ ለመክሰስ፣ ሀብት ለማፍራትና ባለቤት ለመሆን፣ ለመያዝ ያልተገደበ ሥልጣን (capacity) ያለው መሆኑ፣
- ልክ ሌሎች በሕግ የተቋቋሙ የኮርፖሬት አካላት በሕግ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ለማከናወን ኃላፊነት ያለበት አካል መሆኑ፣
- ታክስ የመክፈል ግዴታ የሌለበት አካል መሆኑ፣ በማናቸውም ሁኔታ የሽርክና ማኅበሩ አባላት በድርጅቱ አማካኝነት ባገኙት ገቢ ለድርብ ድርብርብ የገቢ ግብር የማይዳርጋቸው መሆኑ፣
- የሚመሠረተው ቢያንስ በሁለት ሰዎች ሆኖ በአባልነት በሚያቅፋቸው አባላት ላይ ጣሪያ/ወሰን የሌለው መሆኑ ዋና ዋናዎቹ መለያ ባሕሪያቱ መሆናቸውን አመልክተዋል፡፡

አቶ ታምሩ LLP ከላይ የተዘረዘሩት ጠባዮች ከተራ የሽርክና ማኅበር እንደሚለየው እና ከሌሎቹ የሽርክና ማኅበራት ለጠበቆች ድርጅትነት ተስማሚ መሆኑን በማመልከት ይህን ሞዴል መከተል እንደሚቻል በመጠቆም ገለፃቸውን አጠቃልለዋል፡፡

የአቶ ታምሩ ገለባ እንዳበቃ አወያዩ አቶ ጌታቸው ቅጣው አፄ ምኒሊክ የCaputulation Treatyን በተፅዕኖ መቀበላቸውን በማስታወስ አሁንም በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን ለማፍሰስ የቅድሚያ ጥናት እያደረጉ ያሉ ባለሀብቶች በኢትዮጵያ የጠበቃ ድርጅቶች ባለመኖራቸው ያሉት ግለሰብ ጠበቆች በመሆናቸው በግለሰቦች ላይ እንደማይተማመኑ በዚህ የተነሳም የየራሳቸውን legal firms ይዘን እንመጣለን በማለት ላይ መሆናቸውን፣ አገር በቀል ጠበቆች ሳይደራጁ እና አንድ ደረጃ ላይ ሳይደርሱ እነዚህ የውጭ ሀገር legal firms የሚገቡ ከሆነ የሀገር በቀል ጠበቆች ሕልውና አደጋ ላይ እንደሚወድቅ እና ጉዳዩም የግለሰብ ጠበቃ ሕልውና ጉዳይ ብቻ ሳይሆን ከሀገር ሉዓላዊነት (Sovereignty) ጋር የሚያያዝ እና ሊተጋበት የሚገባ ጉዳይ መሆኑን በማሳሰብ የሚቀጥለውን አቅራቢ አቶ መሥፍን ታፈሰን የመወያያ ጽሑፋቸውን እንዲያቀርቡ ጋብዘዋቸዋል፡፡ አቶ መስፍንም የጥብቅና አገልግሎት ሰጭ ድርጅቶች አስፈላጊነትና አስተዳዳር ላይ ያተኮረ ጽሑፍ ለማዘጋጀት ለ20 ጠበቆች መጠይቅ ተዘጋጅቶ መብቱንና ከዚህም 10 ያህል ምላሽ ማግኘታቸውን የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊዎችን ቃለ-መጠይቅ ማድረጋቸውን እና መጠይቅም ማስሞላቸውንም አመልክተዋል፡፡

የመወያያ ጽሑፉን ዓላማ በተመለከተ አቶ መስፍን ሲናገሩ በዋነኛነት ለምምክሩ መነሻ የሚሆኑ ጥያቄዎችን ለማንሳት ያለመ መሆኑን አመልክተዋል፡፡ አቶ መስፍን በዚህ ውይይት ላይ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ምን እንደሆነ በጽሑፋቸው አመልክተዋል፡፡ እነዚህም፡-

1. አሳዛኙ የዛሬው የጠበቃው ሥዕል ምን ይመስላል?
2. ጠበቃው ባለመደራጀቱ ያጣው ምንድን ነው?
3. እስከአሁን ጠበቆች ለመደራጀት ለምን አልቻልንም?
4. የወደፊቱ ተስፋችንስ ምንድን ነው? የሚሉ መሆናቸው በገለፃቸው ጠቁመዋል፡፡

አቶ መስፍን አሁን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመዳሰስም የሚከተለውን ብለዋል፡፡

- ኢኮኖሚው በመለወጥ ላይ መሆኑን፣
- ባለሀብቶች ሀብታቸውን በሥራ ላይ ከማዋላቸው በፊት የጥብቅና Risk Assessment የሚሠሩ መሆኑን፣
- የደራ ነገር ግን የተዘበራረቀ የጥብቅና አገልግሎት ገበያ እየተፈጠረ መሆኑን፣
- ባለሙያው በብዛት ወደገበያው እየገባ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የጥብቅና አገልግሎት ሥራን ለመሥራት የሚያስፈልጉ ነገሮችን በተመለከተም አቶ መስፍን የሚከተለውን ብለዋል፡፡

- ሥራው ካፒታል የማይጠይቅ መሆኑን፣
- የሥራ ልምድ እንደሚያስፈልግ፣
- የውል ስምምነት፣ የጥብቅና ካባ፣ ኮምፒውተርና አጀንዳ ለአንድ ጠበቃ ቁልፍ ነገሮች መሆናቸውን፣
- ቀጠሮን በመጠበቅ ረዥም ሰዓት ለማባከን ትዕግሥት መኖርን ጠቃቅሰዋል፡፡

ወደ ሥራው ከተገባ በኋላ የሚስተዋሉ ለውጦችን በተመለከተም፡-

- ቢሮ መከራየት/የመኖር እና ፀሐፊ የመቅጠር፣
- መኪና፣
- የክርክር/የምክር መዛግብት፣
- መጉምራት፣ ሌሎች ንብረቶችን ማፍራት ድሎች እና ሽንፈቶችን መቀበል፣

አቶ መስፍን አንዳንድ ክስተቶች ባሉት የጽሑፋቸው ክፍል በጠበቃው መካከል ከአብሮ መሥራት ይልቅ አብሮ መብላት የሚያመዝን መሆኑን፣ ፍፃሜያቸው በአለመግባባት እና በጠብ የተጠናቀቁ በኅብረት የመሥራት ሙከራዎች እንደነበሩ ጠቁመዋል፡፡

አቶ መስፍን አያይዘውም በኦሮሚያና በደቡብ ክልሎች የጠበቃ ድርጅቶችን ለማቋቋም በአዋጅ የተፈቀደ ቢሆንም በተግባር ግን የተመዘገቡ የጠበቃ ድርጅቶች አለመኖራቸውን በጽሑፋቸው አመልክተዋል፡፡

ከጥብቅና ድርጅት ጋር በተያያዙ መንግሥታዊ አቋሞች ናቸው ያሏቸውን ጉዳዮችም አቶ መስፍን በማብራሪያቸው ነካክተዋል፡፡ እንደሳቸውም አተያይ የመንግሥት አቋም ፈቃድ የምታወጡበትን ሥርዓት ዘርግቻለሁ፣ አከታትላችኋለሁ ከመስመር ስትወጡም አስተካክላችኋለሁ የሚል ነው ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ፡-

- እንደሙያ ድርጅት ሳይሆን አንድ፣ ሁለት፣ ሦስት ሆኖ የመሥራት መብት አልተከላከለም፣
- የጥብቅና ድርጅት ለማቋቋም የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች ላይ ጥናት በመካሄድ ላይ መሆኑ፣ ዝግጅትም መኖሩን አቶ መስፍን አንስተው አሁን በድምር ላይ ያለው ሁኔታ ሁሉም ለራሱና በራሱ ዛቢያ ዙሪያ እየሮጠ፣ በVicious Circle ውስጥ ያለ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

አቶ መስፍን የጥብቅና ሥራ አጀማመርና ሂደት በአራት እንደሚከፈሉ አመልክተዋል፡፡ እነዚህም፡-

- መደናገጥ እና መሯሯጥ፣
- መደላደል፣
- መወየብ እና
- መጥፋት

የጥብቅና አገልግሎት አሉታዊ ገፅታውን በተመለከተም አቶ መስፍን ሲናገሩ አሁን እውቀትና ክህሎት ሳይሆን "ማንን ታውቃለህ? እንዴት ታሸንፋለህ" የሚለው በመሆኑ የሙያውን ልዕልና እና ክብር ማጣት አመላካች እንደሆነ፣ አዲስ ትውልድ የማይፈጠርበት እና ሙያው የማያድግበት ደረጃ ላይ መድረሱን በገለፃቸው አመልክተዋል፡፡

ተደራጅተተን ባለመሥራታችን ያጣናቸው ነገሮች የሚሏቸው ምን እንደሆኑም አቶ መሥፍን ለመጠቋቆም ሞክረዋል፡፡ የጥብቅና ድርጅት አያስፈልግም የሚል አንድም ባለሙያ ያላገጠማቸው መሆኑን ያስታውሱት አቶ መሥፍን ይህም የመደራጀትን አስፈላጊነት እና የማያስገኘውን ጥቅም እንደሚጠቁም፣ መደራጀትም ቀጣይነት ያለው የማያቋርጥ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል መሆኑን፣ ጥልቅ እውቀትን (specialization) የግድ የሚልና ባለሙያውም በአንድ መስክ እንዲያተኩር የሚያደርግ መሆኑን፣ ለፍትሕ ሥርዓቱ እድገትም የተሻለ አስተዋጽኦ ለማበርከት እንደሚያግዝ፣ ለእውቀት ግንባታና ለቡድን ሥራ መሠረት የሚጥል መሆኑን ከሚያስገኟቸው ጥቅሞች መካከል ጥቂቶቹ መሆናቸውን አስታውሰው በተለይም ከሂሳብ አያያዝና ከግብር ጋር የተያያዙ ጥቅሞች እንዳሉት፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ከመጋራት እንዲሁም ትልልቅ የሆኑ ሥራዎችን ለመሥራት ጠቃሚ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

የጥብቅና አገልግሎት በድርጅት መልክ መስጠት አለመቻሉን በተመለከተም በፖሊሲ ረገድ አዋጅ ቁጥር 199/92 አንቀፅ 18 የጥብቅና አገልግሎትን በድርጅት መልክ ለማካሄድ የሚፈቅድ በመሆኑ በመንግሥት በኩል ሙሉ የፖሊሲ ድጋፍ እንዳለው መገንዘብ የሚቻል መሆኑን ነገር ግን

ይህንን ሥራ ላይ ለማዋል ዳተኝነት እንደሚስተዋል የፍትሕ ሥርዓቱት ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ የጠበቆች የአገልግሎት አሰጣጥ ይህ ነው የሚባል ቦታ አለማግኘቱ ጉዳዩ ትኩረት ላለማግኘቱ አንድ ማሳያ ነው ብለዋል፡፡ አያይዘውም ምንም እንኳ የጠበቆች ድርጅት ማቋቋም አያስፈልግም የሚል ባለሙያ ያላገኙትን ያህል በተግባር ግን የሚታየው በጠበቆች ዘንድ በራስ እና ለራስ የመሥራት ሥር የሰደደ አዝማሚያና ባሕል መኖሩን በዚህ የተነሳም በጠበቆች ዘንድ የጠበቆች ድርጅቶችን የማቋቋም አጀንዳ አንገብጋቢ እንዳይሆን የበኩሉን አስተዋጽኦ ማድረጉን አመልክተዋል፡፡ የአፈፃፀም ክፍተት መኖሩን የጠቆሙት ጽሑፍ አቅራቢው ይመለከታቸዋል ያሏቸው የመንግሥት አካላት ከሕግ ባለሙያዎች የጥብቅና አገልግሎት ድርጅት የማቋቋም ጥያቄ ሲቀርብላቸው የሚሰጡት ምላሽ ዝርዝር ሕግ እስኪወጣ ጠብቁ የሚል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የጠበቆች አገልግሎት ድርጅቶች ቢቋቋሙ በምን መልክ ነው ተቆጣጣሪው አካል ሊቆጣጠር የሚችለው? ለዚህ ተግባር ዝግጁ ነውን? ለሚለው ጥያቄም በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት በኩል የሚሰጠው ምላሽ ይህ የእኛ ሥራ አይደለም የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ቢጠናከር ለዚህ ጥያቄ መልስ ሊሰጥ ይችላል የሚል እንደሆነ አቶ መስፍን ገልፀዋል፡፡

መደራጀት ለምን? የሚል ጥያቄ አንስተው የራሳቸውን ምላሽ የሰጡት አቶ መሥፍን ጥያቄውን ከፖለቲካ፣ ኢኮኖሚ እና ማኅበራዊ ሁኔታዎች አኳያ በመመርመር መልስ ነው ያሉትን ለተሳታፊው ጠቁመዋል፡፡

ከፖለቲካ አኳያ ባለሙያዎች በተናጠልም ሆነ ተደራጅተው ሠርተው የመኖር ሕገ-መንግሥታዊ መብት ያላቸው መሆኑ ባለሙያዎች ተደራጅተው ለመሥራት የሚከለክላቸው ነገር አለመኖሩን፣ ከኢኮኖሚ አኳያ አሁን በአገሪቱ ላይ የሚታየው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የውጭ ባለሀብቶችን እየጋበዙ መሆኑን፣ የውጭ ባለሀብቶችም ዘንድም ጥራት ያለው የሕግ አገልግሎት ፍላጐት ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መሄዱን አቶ መስፍን አመልክተዋል፡፡

ከሕግ አገልግሎት አቅራቢዎች አንፃር የሕግ ትምህርት ተቋማት የባለሙያዎች ምንጭ ሆነው ሲያገለግሉ መቆየታቸውን ለወደፊቱም ይህንኑ ተግባር እንደሚቀጥሉ፣ ግለሰብ ጠበቆች፣ የመንግሥት ተቋማት ነገረ ፈጆች፣ የበጐ አድራጐት ድርጅቶች የሕግ አገልግሎት አቅራቢዎች መሆናቸውን ለወደፊቱ የጠበቆች አገልግሎት ድርጅቶች ሚና ሊኖራቸው እንደሚችሉ ጠቅሰው የሕግ አገልግሎት ተጠቃሚዎቹ ዜጐች የችግሩም ገፈት ቀማሾቹ እነርሱ መሆናቸውን ጽሑፍ አቅራቢው አመልክተዋል፡፡

የሕግ አገልግሎትን ከመቆጣጠር አንፃር ኃላፊነት ያለበት የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት መሆኑን ይህ አካልም የጠበቆች አገልግሎት ድርጅቶችን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ ረቂቅ ሕጐች ያሉት መሆኑን ለወደፊቱ ግን ሙያተኞችን የመቆጣጠር ሥራ በሕግ ተቋቁመው ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ ማኅበራት ሲቋቋሙ ይህንን ኃላፊነት ሊወስዱ የሚችሉበት እድል መኖሩን አቶ መስፍን አብራርተዋል፡፡

የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቶችን ለማቋቋም የድርጅቱ አባላት መኖር አስፈላጊ መሆኑን የጠቀሱት አቶ መስፍን በዚህ ድርጅት አባል ለመሆን ከሚያስፈልጉ ነገሮች በቅድሚያ ጠበቃ መሆን፣ የሕግ ባለሙያ ያልሆኑ ሌሎች ባለሙያዎች፣ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች ናቸው ብለዋል፡፡ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱን ቅርፅ በተመለከተም በክልል ሕጐችም ሆነ አሁን እየተረቀቁ ባሉ ሕጐች ተራ የሽርክና ማኅበር ተደርጐ እንደተቀመጠ ነገር ግን የኦሮሚያ ሕግ የኀብረት የሽርክና ማኅበር አድርጐ ማስቀመጡን፣ የተሻሻለው ረቂቅ የንግድ ሕግ ሊሚትድ ሊያቢሊቲ ፓርትነርሺፕ አድርጐ መደንገጉን ሆኖም ረቂቅ ሕጉ የጠበቆች አገልግሎት ድርጅቶች የሚመራው በጠበቆች ብቻ ነው የሚል ገደብ ማስቀመጡን፣ ታክስን በተመለከተም Firmን ሳይሆን ግለሰብ አባላትን

የሚመለከት አድርጐ መደንገጉን፣ ኃላፊነትን በተመለከተ ኩባንያው እንዲወስድ ነገር ግን በቸልተኝነት ለተፈፀመ ጉዳት የተናጠልና የጋራ ኃላፊነት (Joint & Several Libility) እንዲያስከትል ተደርጐ ድንጋጌው መቀረፁን አቶ መስፍን አመልክተዋል፡፡ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቶችን በተመለከተ መንግሥትን ከመጠበቅ (Reactive ከመሆን) ማኅበሩ በራሱ ተነሳሽነት (proactive) ሚና ሊኖረው ይችላልን? ሲሉ ጉዳዩን በጥያቄ መልክ አንስተዋል፡፡

## ውይይት

አወያዩ የመንግሥት አካላትን ወክለው የተገኙ ካሉ ቅድሚያ እንደሚሰጡ ባስታወቁት መሠረት ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የመጡት ተወካይ በጠበቆች አስተዳደር ስም የውይይቱን አዘጋጆች ካመሰገኑ በኋላ የተጀመረው ጥረት ቀጥሎ በተዘጋጁት ረቂቅ ሕጐች ላይ ውይይት እንዲደረግ ለዚህም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በተለይም የጠበቆች አስተዳደር "የናንተን ተነሳሽነት ለመደገፍ ፍላጐት ስላለን ግፋበት" ብለዋል፡፡

ከኦሮሚያ ፍትሕ ቢሮ የመጡት አቶ ተክሉ በዚህ አገራዊ በሆነ ጉዳይ ላይ ተወያይቶ አቅጣጫ ማስቀመጡ በጐ ጅምር መሆኑን፣ በኦሮሚያ ክልልም በአዋጅ ቁ. 182/05 የጥብቅና አዋጅን አሻሽሎ Law Firm ማቋቋም እንደሚቻል መደንገጉን አመልክተዋል፡፡ አያይዘውም በክልልም በፌደራል ደረጃ የሚሠሩ ወደ 1000 የሚጠጉ ጠበቆች በኦሮሚያ መኖራቸውን፣ Law Firm ማቋቋም እንደሚቻል በአዋጅ ቢደነገግም እስከአሁን ድረስ ይህንን የጠበቆች አገልግሎት ድርጅት ለማቋቋም የመጣ ጠበቃ አለመኖሩን ተናግረዋል፡፡ እንደአቶ ተክሉ ገለፃ ከልምድ በመነሳት የጥብቅና ሥራ ከቡድን ይልቅ በግለሰብ ደረጃ የመሥራት ዝንባሌ ያለ ይመስላል ካሉ በኋላ አሁን ያለውንም አዋጅ ከአገር አቀፍ ተሞክሮ በመቅሰም ሊሻሻል እንደሚችል ጠቁመዋል፡፡ የPro bono አገልግሎት ደካማ መሆኑን የገለፁት ተሳታፊ ይህንን አገልግሎት ሥርዓት ለማስያዝም ሆነ ለሀገር እድገት የጠበቆች አገልግሎት ድርጅት መቋቋም ጠቃሚ መሆኑን በማመልከት አስተያየታቸውን አጠቃልለዋል፡፡

አቶ ፋሲል ስለሺ በሰጡት አስተያየት የጠበቆች አገልግሎት ድርጅት ጠቀሜታው ምንድን ነው? የሚለው በደንብ ባልተብራራበት ሁኔታ ይቋቋም ብሎ መናገር አሁን ያለሁበትን ምቾት (comfort) ስለሚነካ ተጠቃሚ ልሆን አልችልም፡፡ እንደ አቶ ታምሩ ያሉ ለዓመታት በሙያው ስማቸውን የገነቡ ሰዎች እኔን፣ ሌሎች ጀማሪዎችን በሚያቋቁሙት Law Firm ያቅፋሉ? ከLaw Firm መቋቋም ጐን ለጐን በግል የጥብቅና መሥራት ይቻላል? የLaw Firm መቋቋም ተግባራዊ ቢሆን እንመዘገባለን ወይ? አሁን የተናገሩት የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ተወካይ በገቡት ቃል ላይም ጥርጣሬ አለኝ በማለት ጥያቄና አስተያየታቸውን አጠቃልለዋል፡፡

አቶ ስለሺ ቀፀላ አስተያየታቸውን መስጠት የጀመሩት እንደሩዋንዳ ካለ ትናንሽ አገሮች አንሰን በሕግ ተቋቁሞ ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ጥርስ ያለው የጠበቆች ማኅበር እስካሁን ልንመሠርት አልቻልም፡፡ የLaw Firm እንዲቋቋም ጥረት ሲደረግ የነበረው የኦሮሚያ ክልል ይህንን የሚመለከት ሕግ ከማውጣቱ በፊት ነበር፡፡ Law Firm እንዲቋቋም የውትወታ፣ የማግባባት ሥራዎችን ስንሰራ ቆይተናል፡፡ ከኛ የቀረ ነገር የለም ካሉ በኋላ የLaw Firm መኖር ግለሰቦች በግላቸው የጥብቅና አገልግሎት ከመስጠት አያግዳቸውም ብለዋል፡፡ አቶ ስለሺ የLaw Firm አመሠራረትን በተመለከተም ሲናገሩ የጥብቅና አገልግሎት ድርጅቱን የሚፈልጉ እና ፍላጐት ያላቸው ባለሙያዎች ተመራርጠው እንደሚያቋቁሙት አመልክተው በLaw Firm መደራጀት የተሻለ አገልግሎት ለመስጠት እንደሚያስችል፣ የLaw Firm አለመኖር የተለያዩ ለሀገራችን የሚጠቅሙ እድሎችን እንደሚያሳጣ አመልክተው የLaw Firm እንዲቋቋም በመንግሥት አካላት ዘንድ ፍላጐት አለወይ? የፌደራል መንግሥት አዋጁን ለማስፈጸም ዝርዝር መመሪያ ለማውጣት ለምን ዳተኛ ሆነ? የሚል ጥያቄ በመሰንዘር ንግግራቸውን አብቅተዋል፡፡

ለመሆኑ ማኅበሩ አለን ወይ? በሚል ጥያቄ ንግግራቸውን የጀመሩት የኢትዮጵያ የጠበቆች ማኅበር ፕሬዚዳንት አቶ በሻዳ ገመቹ መልሱ በክልልም ሆነ በፌደራል ደረጃ ያሉት ማኅበራት በጥቂት ሰዎች ጥረት የሚንቀሳቀሱ ተቋማት እንጂ ትርጉም ያለው ሥራ የሚያከናውኑ ማኅበራት የሉንም። መጠየቅ ያለብን ራስን በራስ የሚያስተዳድር ማኅበር ለማቋቋም ለምን አቃተን? እንዲህ ዓይነቱ ማኅበር እንዲኖረን ምን ያህል ተግተናል? ጥረትስ አድርገናል? እንዲህ ዓይነት ማኅበር ኖሮን ቢሆን ኖሮ Law Firm ለማቋቋም ይህን ያህል ጊዜ ባልፈጀብን ነበር ብለዋል። አስተያየታቸውንም በመቀጠል ጉዳዩ የፈቃድ አሰጣጥ ጉዳይ ስለሆነ አሁንም እየጠበቅን ያለነው የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መ/ቤትን ነው ካሉ በኋላ በፌደራል ደረጃ የሚሰጠው ፈቃድ ክልል ላይ ይሠራል? ወይስ ለክልልም ሌላ ፈቃድ ማውጣት ይጠበቅብናል? ወይስ አንድ ማዕከል (Central Register) ነው የሚኖረው? የሚሉ ጥያቄዎች ግልፅ የሆነ ምላሽ እንደሚያስፈልጋቸው አመልክተዋል። የLaw Firm መኖር የሥነ-ምግባር ችግርን ለመቅረፍ፣ ሙያውን ለማሳደግ ጠቃሚ መሆኑን የገለፁት አቶ በሻዳ ማነው Law Firmን የሚያስተዳድረው? የፈቃድ አሰጣጡ ምን መልክ መያዝ ይኖርበታል? የአደረጃጀቱ ሁኔታስ ምን መምሰል አለበት? የሚሉና ሌሎች ተያያዥ ጥያቄዎችን ለመፍታት ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት ጋር ብቻ ሳይሆን ከየክልሎቹ የፍትሕ ቢሮዎች ጋር ተቀራርቦ መሥራት እንደሚያስፈልግ በመጠቆም አስተያየታቸውን አብቅተዋል።

የLaw Firmን መኖር ጠቀሜታ ለማሳየት ባለቤቴ ወልዳ እቤቴ ትቼያት ቀጠሮ ስለነበረብኝ ፍ/ቤት ለመሄድ ተገድጃለሁ በማለት ንግግራቸውን የጀመሩት አቶ አብደላ የተባሉ ተናጋሪ አስከሬን እቤት አስቀምጠው ፍ/ቤት የተኬደበት አጋጣሚ አለ፣ በግል ምክንያት በቀጠሮ ቀን ጠበቃ በችሎት ያለመቅረብ ምንም ይቅርታ ስለሌለው የLaw Firm መኖር እንዲህ ዓይነቶች ድንገተኛ ክስተቶች ጠበቃ ከችሎት ቢቀር ሌላ ሰው ሊተካበት እንደሚችል ለተሳታፊው በመግለጽ የLaw Firm መኖርን አስፈላጊነት ለማሳየት ሞክረዋል። አቶ አብደላ አስተያየታቸውን በመቀጠል አዲሷ አገር ደቡብ ሱዳን ውስጥ የdocument authentication ሥራ ጠበቆች ይሠራሉ። እኛ አገር ግን ይህ አይደረግም ካሉ በኋላ በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ለውጥ እየተካሄደ መሆኑን እና ግዙፍ ኩባንያዎች ወደ ሀገሪቱ በመግባት ላይ መሆናቸውን እንዲህ ዓይነቶቹን ኩባንያዎች እየመጡ ባሉበት አገር በአፋጣኝ ተደራጅተን መጠበቅ ይኖርብናል የሚል አስተያየት ሰንዝረዋል።

## የጽሑፍ አቅራቢዎቹ ምላሽ

## አቶ ታምሩ ወንድምአገኘሁ

እስካሁን ሲሰጡ በቆዩት አስተያየቶች እንጂ ጥያቄዎች ባለመሆናቸው የምሰጠው መልስ አይኖርም በማለት ንግግራቸውን የጀመሩት አቶ ታምሩ የLaw Firmን በሚመለከት ሁሉንም ጉዳዮች በዚህ ስብሰባ መጨረስ አመለመሆኑን አመልክተዋል። የspecialization አስፈላጊነት የLaw Firmን መኖር አስፈላጊ እንዳደረገው፣ በአሁኑ ወቅት የአእምሯዊ ንብረት ጥበቃ ትልቅ የሕግ ዘርፍ እየሆነ መምጣቱንና በአገራችን Patentን የሚሞላ ጠበቃ አለመኖሩን፣ የኮንስትራክሽን ሕግ፣ የመርከብ ሕግ ወዘተ ልዩ ሙያ የሚጠይቁ ዘርፎች መኖራቸውን፣ ለእንዲህ ዓይነቶቹ ልዩ ሙያ ለሚጠይቁ ሥራዎች Law Firm መልስ እንደሚሰጥ አመልክተዋል። በኢትዮጵያ Legal Certainity እንጂ Judicial Certainity አለመኖሩን ያወሱት አቶ ታምሩ የLegal Firm መኖር ይህንን ችግር እንደሚፈታው አመልክተዋል። የLaw Firm አባልነትን በተመለከተ ሲናገሩም ይህ የሚመራው በኢኮኖሚ ሕግ መሠረት በመሆኑ ዝም ብሎ የሚገባበት እንዳልሆነ አመልክተዋል። አቶ ታምሩ በኢትዮጵያ ከ1934-1967 ድረስ በጥብቅና አገልግሎት እያደገ የሄደበት ዘመን እንደነበር አስታውሰው ከዚያ በኋላ የተዘረጋው የሶሻሊስት ሥርዓት የንብረት ባለቤትነት መብት (Property Right) ሰለባ የሆነበት ስለነበር ጠበቃ ሊወጣበት እንዳልቻለ አመልክተዋል። አቶ ታምሩ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ከሐኪሞች ጋር ተነፃጽሮ በቀረበው አስተያየት ላይም የሚከተለውን

ብለዋል፡፡ ለማኅበራችን በመልካም ምሣሌነት መውሰድ አለብን ብዬ የማስበው የሀኪሞችን ማኅበር ሳይሆን የኢትዮጵያ የንግድ ሥራ ት/ቤት ተማሪዎች ማኅበርን ነው፡፡ ጠንካራ ማኅበር በመሆኑ የራሱ የሆነ ጽ/ቤት ያለው ነው በማለት ንግግራቸውን አጠቃልለዋል፡፡

## አቶ መስፍን ታፈሰ

"የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበር ጠንካራ ነው አይደለም" የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ራሱን የቻለ ጥናት እንደሚያስፈልግ በመጥቀስ ንግግራቸውን የጀመሩት አቶ መሥፍን በምድር ላይ ካሉት ተግዳሮቶች አኳያ የማኅበሩ አባላትና መሪዎቹ እያደረጉ ያሉት ጥረት እያበረከቱት ያለው አስተዋጽኦ ሊወደስ ይገባል ብለዋል፡፡ አቶ መስፍን የDevelopment እና Underdevelopment መኖር አለመኖር ምክንያቱ በጠንካራ መሠረት ላይ የተገነቡ ጠንካራ ተቋማት በመኖር አለመኖሩ ላይ ነው፡፡ እንግሊዝ የተፃፈ ሕገ-መንግሥት የላትም ነገር ግን ጠንካራ ተቋማትን መፍጠር በመቻሏ አሁን ያለችበት ደረጃ ደርሳለች፡፡ እኛንም እዚህ ያሰባሰበን ተቋም የመመሥረት ጉዳይ መሆኑን በአገራችን Law Firm እንደተቋም አለ? የለም? የሚለውን ለማየት መሆኑን አመልክተዋል፡፡ ኢትዮጵያ ፌደራል ሥርዓት የዘረጋች ሀገር መሆኗን ያስታወሱት አቶ መስፍን ሥራዎቻችን የተለያዩ ተዋንያን የሚሳተፉባቸው፣ የሚሠሩትም ክልሎች ላይ በመሆኑ ከክልሎች ጋር ተቀናጅቶ መሥራት የግድ መሆኑን አስምረውበታል፡፡ አቶ መስፍን የእውቀት መፍለቂያ ተቋማትን በማጠናከር ትኩረት የሚሻ ጉዳይ መሆኑን በንግግራቸው አመልክተዋል፡፡ ተቋማትን የመፍጠርና የማጠናከርን አስፈላጊነት በተመለከተ አወያዩ አቶ ጌታቸው ቅጣው በምሳሌነት ያቀረቡት የአቶ ተሾመ ገብረማርያምን ሁኔታ ሲሆን አቶ ተሾመ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ defacto የሕግ ቢሮ እንደነበራቸው አስታውሰው እርሳቸው ከእዚህ ዓለም በሞት ሲለዩ ይህ ቢሮ መፍረሱን እና ይህ አሳዛኝ ሁኔታ ሊከሰት የተቻለው ተቋም መመሥረት ባለመቻሉ እንደሆነ አመልክተዋል፡፡ አያይዘውም Law Firm መቋቋም አስፈላጊ ከሚያደርጉት ምክንያቶች አንዱ ውጤታማ ሥራ ሲሠሩ የቆዩ የሕግ ቢሮዎች ከባለቤታቸው ሕልፈት ጋር አብረው እንዳይሞቱ ለማድረግ ጭምር መሆኑን የነዚህ ተቋማት ቀጣይነት ለሀገር ጠቃሚ በመሆኑ ይህንን ተልዕኮ እውን ማድረግ ግዴታችን ይሆናል ብለዋል፡፡

ስለ Law Firm ለጠበቃው መንገርና ማስረዳት አስፈላጊ መሆኑን የገለፀችው አንዲት ተሳታፊ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርም Law Firm እውን ይሆን ዘንድ መንግሥት አስፈላጊውን ሥራ እንዲሠራ መገፋፋት ይኖርበታል፡፡ ጠበቃውም አሁን እየመጣ ካለው የመዋዕለ ንዋይ ፍሰት የLaw Firm በማቋቋም ተጠቃሚ መሆን አለበት ብላለች፡፡

መቅደስ መዝገቡ በበኩሏ የመንግሥት መ/ቤቶች የተለያዩ ዓለም አቀፍ Law Firm በአማካሪነት ሲቀጥሩ ይታያል፡፡ እነዚህ ዓለም አቀፍ የLaw Firm የሀገሪቱን ሁኔታ፣ ሕጐቹን የሚያውቁትን የሀገሪቱን ጠበቆች sub-contract በማድረግ ይሠራሉ፡፡ Law Firm ቢኖር ኖሮ ምናልባትም ሥራው ለውጭ Law Firm መስጠት ላያስፈልግ ይችላል፡፡ እና ይህም መታየት ይኖርበታል በማለት አስተያየቷን ሰጥታለች፡፡

አቶ ደሳለኝ በርኼ ከጆስቲስ ፎር ኦል ፕሪዝን ፌሎውሺፕ በሰጡት አስተያየት ባለፈው ወር በኢሕባማ እና በኢትዮጵያ ጠበቆች ማኅበር መካከል የመግባቢያ ስምምነት መፈረሙን አስታውሰው በመግባቢያ ስምምነት ከተዘረዘሩት እና በሁለቱ ማኅበራት በጋራ ሊከናወኑ ከታሰቡት ተግባራት አንዱ Law Firm እውን ስለሚሆንበት ሁኔታ እንደሆነ በመጥቀስ ፕሪዝን ፌሎውሺፕ ይህንን ሥራ ለመደገፍ ፈቃደኛ መሆኑን አመልክተዋል፡፡

አቶ ታምራት ኪዳነማርያም ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በሕግ የተቋቋመና ራሱን በራሱ የሚያስተዳድር ማኅበር ለማቋቋም ፈቃደኛ መሆኑን ገልጿል፡፡ በተመሳሳይም የLaw Firm

በማቋቋም አስፈላጊነት ላይም ድጋፋን ገልጿል። ስብሰባው ከመጠናቀቁ በፊት ለLaw Firm ማቋቋሚያን የሚመራ ረቂቅ ለማዘጋጀትና ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት ለማቅረብ ስምምነት ላይ ብንደርስ የሚል ሃሳብ አቅርበዋል። አቶ ታምራት ንግግራቸውን በመቀጠልም ከእኔ በፊት የነበሩት ተናጋሪዎች እንዳመለከቱት እኛ ኢትዮጵያውያን ጠበቆች ሥራችንን እየተቀማን ነው። የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሕግ ለማውጣት ጨረታ ሲያወጡ የውጭ ሀገር Law Firms ጨረታውን በማሸነፍ እየሠሩ ይገኛሉ። የአገሪቱን ሕጐች የምናውቀው እኛ ሆነን ሳለ አርቢትሬሽን ላይ ስንሳተፍ አንታይም። እነዚህ እነዚህ ሁኔታዎች የLegal Firm መቋቋምን አስፈላጊነት ግልፅ ያደርጉታል ብለዋል።

አቶ ኃይሉ ቡራዩ በበኩላቸው የንግድ ሥራ እየሠራ ነው አይደለም? የሚል ጥያቄ ካነሱ በኋላ ለምንድን ነው በኩባንያ መልክ የማንደራጀው? ለምን በLLP መደራጀት አስፈለገ? የሚል ጥያቄ ሰንዝረዋል።

ስሙን ያልገለፀ አንድ ተሳታፊ Legal Firm ባለመኖሩ ያጣነው ብዙ ነው። ለአገልግሎታችን የምንጠይቀው ክፍያ በየግላችን በመሆኑ ወጥነት ይጐድለዋል። የምንሰጠው አገልግሎትም ቡራቡሬ በመሆኑ ከውጭ የሚመጡ ባለሀብቶችን እምነት እየሸረሸርነው ነው። ኬንያ ካሉ ጠበቆች አንፃር እኛ የምናስከፍለው የአገልግሎት ክፍያ ምን ያህል ነው? አዋጁ Law Firm ማቋቋምን ይፈቅዳል። ነገር ግን እስከአሁን ተፈፃሚ አልሆነም። ገፍቶ መሄድ ያስፈልጋል። አሁን እዚህም እዛም የምናያቸው defacto Law Firms በሙከራ ላይ ናቸው። አሁን በተግባር የሚታየው ነገር የምንሠራው ሥራዎች ተመሳሳይ ናቸው አዲሱም 20፣ 30፣ 40 ዓመትም የሠራው ጠበቃ አንድ ዓይነት ሥራ ነው እየሠሩ ያሉት። ጥያቄው መሆን ያለበት አሁን ያለንበትን ሁኔታ ለመለወጥ ምን ዓይነት እርምጃ ነው መወሰድ ያለበት የሚለው ነው። ሌላው መታወቅ ያለበት የጥብቅና ሥራ ከፍርድ ቤት ጋር ብቻ የተያያዘ አይደለም። ከዛ የዘለለ እና የሚጠቅሙ ብዙ ሥራዎች አሉ። የጥብቅናን አገልግሎት ከፍርድ ቤት ጋር ከሚያያይዘው አመለካከት መውጣት ይኖርብናል። እስከአሁን የተነጋገርንባቸውን ነገሮ ወደመፍትሔ እንዴት እንደምንወስደው ብንነጋገር መልካም ነው በማለት አስተያየቱን አጠቃልሏል።

ከአአዩ ሕግ ት/ቤት የመጣ ባለሙያ ወደ ሥራ እንዴት እንግባ? LLP እስኪወጣ እንጠብቅ? የሚል ጥያቄ አንስቶ መጠበቅ የሚያዋጣ አይደለም። ምክንያቱም ሂደቱ ረዥም ጊዜ የሚፈጅ በመሆኑ ነው ብሏል። አያይዞም ለሕግ ባለሙያዎች በሚጠቅም መልክ ሕጉ እንዲወጣ ምን እንሥራ? አጭሩ መንገድ በጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ የሚወጣው መመሪያ በመሆኑ እሱ ላይ ማተኮሩ ይበጃል። ሆኖም ይህን ለመፈፀም ኃላፊነትን የሚወስድ አካል መፈጠር ይኖርበታል ብሏል።

ሌላ ተናጋሪ የLegal Firm ጠቀሜታ ምን ያህል ተረድተናል? ይህንን ሥራ የሚሠሩ Steering Committee ቢቋቋም፣ በዚህ ጉዳይ ላይ ለባለሙያው ግንዛቤ ለማስጨበጥ በጆርናል ላይ ቢፃፍ የሚል ሃሳብ አቅርቧል።

አቶ ማንያውቃል መኮንን ወደፊት መሠራት ስላለባቸው ሥራዎች የሚከተሉትን ሃሳቦች ሰንዝረዋል።

1ኛ/ Law Firm ምንድን ነው? አወቃቀሩ እና አስተዳደሩ ምን መምሰል ይኖርበታል? ወዘተ በሚሉ ጉዳዮች ላይ የሚወያይ ሁሉንም አካላት ያካተተ የምክክር ስብሰባ ማካሄድ፣

2ኛ/ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ረቂቅ መመሪያ እያዘጋጀ ስለሆነ በረቂቁ ላይ የግብዓት ማሰባሰቢያ ውይይት ከጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ መ/ቤት ጋር ማዘጋጀት፣

3ኛ/ Regulatory Bodyን ያካተተ እና የፌደራል ሥርዓት በዘረጉ አገሮች የመስክ ጉብኝት ለማድረግና ተሞክሮ ለመቅሰም ከፕሪዝን ፎሎውሺፕ ጋር በመተባበር ቢዘጋጅ የሚል ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

## ማጠቃለያ

አቶ ታምሩ LLP መደራጀት ለምን አስፈለገ? በካምፓኒ መልክ ለምን አንደራጅም? ለሚለው ጥያቄ በኮመን ሎው አገሮች የጠበቆች አገልግሎት a business but not commercial nature በመሆኑ ነው፡፡ አሁን አሁን ይህንን አሠራር የሲቪል ሎው ሀገሮች እየተቀበሉት ነው፡፡ Law Firm አዋጭነቱ ታይቶ ነው የሚቋቋመው፡፡ ከዚህ አንፃር የLaw Firm አንዱ ጥቅም የጡረታ ክፍያ፣ Indeminity ኢንሹራንስ አለው ብለዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥት ከውጭ ኩባንያዎች ጋር ያዋዋላል፡፡ መንግሥት ከነዚህ ኩባንያዎች ጋር ሲሠራ የአገሩን ጠበቆች ከነዚህ የውጭ ፊርሞች ጋር እንዲጣመሩ ቢያደርግ መልካም መሆኑን አቶ ታምሩ ጠቁመዋል፡፡ አያይዘውም የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ 14 ሥልጣኖች አሉት፡፡ እነዚህን ሁሉ ሥራዎች በራሱ መሥራት ይከብደዋል፡፡ ስለዚህ ከጠበቆች ማኅበር ጋር መሥራት ይገባዋል ብለዋል፡፡

አቶ መስፍን በበኩላቸው ሲናገሩ ቀደም ሲል በአቶ ኃይሉ ለምን Law Firm በኩባንያ መልክ አይደራጅም ብሎ ለተነሳው ጥያቄ PLCን ለመመሥረት የገንዘብ እና የቁሳቁስ /in kind contribution/ መዋጮ ይጠይቃል፡፡ Legal Firm ትልቁ ነገሩ ገንዘብ ወይም ቁሳቁስ ሳይሆን ሙያዊ elementቱ ነው፡፡ አንድ አንድ ሴክተር ለብቻው ተነጥሎ መቋቋም የሚገባው ተቋም ነው፡፡ ሌላው ለዩ ጠበባይ partnership interest በደንብ የሚመለከተው መሆኑ ነው፡፡ የፓርትነርስ የገቢ ክፍፍል በአደረጉት አስተዋጽኦ ልክ መሆኑ ሌላው ልዩ ጠባዩ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

አቶ ቴዎድሮስ ምህረት በመዝጊያ ንግግራቸው እስከአሁን የተደረገው ውይይት ከባለሙያው አንፃር ብቻ እንደነበርና የLaw Firm መኖር ከአገልግሎት ተቀባዩ አንፃር ያለው አንደምታ ቢጠና ጥሩ ነው፡፡ የLaw Firm መኖር መንግሥትንም ይጠቅማል፡፡ አራት ሺህ ጠበቃን ከመቆጣጠር Law Firmን መቆጣጠር ይቀላል ብለዋል፡፡ የውጭ Law Firms ሲመጡ ገንዘባችንን በክፍያ መልክ ወደውጭ ያወጣሉ፡፡ ስለዚህም Law Firm መኖር ይህንን ሊያስቀር ስለሚችል አገራዊ አንደምታ አለው፡፡ እኛም በግልም ሆነ ተደራጅተን የመሥራት መብት አለን፡፡ የምንጠይቀውም ይህንን ነው ካሉ በኋላ Legal Firmን በተመለከተ በመጭዎቹ ጊዜያት ውይይት ይኖረናል፡፡ በውይይቱ ላይ የተነሱትን ጉዳዮች አካተን የውይይቱን ጭማቂ ለጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ እናቀርባለን በማለት ንግግራቸውን አጠቃልለዋል፡፡

ውይይቱ ከቀኑ 7፡00 ተጠናቋል፡፡